<u>PANORAMA No. 4</u>

# <u>የትዝብት አድማስ</u>

## <u>ደሃ አደጊቱ</u>

በሀገራችን የገጠሩ ህይወት፥ በተለይም በአርሶ አደሩ ኑሮ ውስጥ አንዲት ላም ጥጃዋን ወይም ፍየል ፥ በግ፥ ግልገሏን ወልዳ ወዲያውኑ ስትሞት ያች እናት አልባ የሆነችው ጥጃ ወይም ግልገል ደሃ አደግ ተብላ በመጠራት ትታወቃለች:: ድሃ አደግ መባሏም የእናት ጡት ሳትጠባ ስለቀረችና የእናትን ወዝ፥ እስትንፋስና እንክብካቤ ተነፍጓት ስለቀረ ነው:: በጫቅልነቷ ጥቂት ሳምንታት ወቅት የእንስሰዋ ባለቤቶች እስክትጠነክር ድረስ የእናቷንም ያህል ባይሆን፥ የቅርብ እንክብካቤ ያደርጉላታል:: በረሃብ እንዳትሞትባቸውም በትንሽ ዕቃ ወተት ይግቷታል:: በሞቀ ታዛ ወይም በጓዳ እያስቀመጡም ከብርድ፥ ከቅዝቃዜ ወይም ከፀሀዩ ግለትና ሞቀቱ ያድኗታል:: በእግሯ መንቀሳቀስ እስከ ምትጀምር ድረስ ይህ ሁሉ ርዳታ ይደረግላታል::

ይህ እንግዲህ በተፈጥሮ አጋጣሚ፥ በእንስሳት የሚከሰት የህይወት ገጠምኝ ሲሆን፥ በአንድ ሀገርና በዜጎችም ላይ ተመሳሳይ ሁኔታ ሊከሰት የሚችልበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል::

ይህ ክስተት በሁለት የታሪክ አጋጣሚዎች በሀገራችን በኢትዮጵያ ላይ በተደጋጋሚ ተከስቷል:: አንደኛው፥ ሀገራችን በ1928 ዓም በኢጣሊያ ፋሽስቶች በተወረረችበት ጊዜ ነበር:: በዚሁ ዓ ም ሀገራችን ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በታሪኳ አንድ የውጭ ወራሪ ኃይል ሁሉ አቀፍ ወረራ አካሂዱባት፥ ብሔራዊ ነፃነቷ ተገፍፎ፥ ሰብዕናዋ በተዋረደበት ጊዜ ነበር:: በዚህ ወቅት መላው የአፍሪካ ሀገሮች በአውሮፓ የቅኝ ገዥዎች ቀንበር ስር የወደቁበት የባርነት ዘመን ስለነበር፥ ሀገራችንን ሊረዳትም ሆነ ሊያዝንላት የቻለ የቅርብ ጎረቤት አልነበረም:: ዋና መስሪያ ቤቱን በስዊትዘርላንድ ከተማ ጀኒቫ ያደረገው፥ የመንግሥታት ማኅበር የተሰኘው ተቋምም ፥ሊረዳት አልቻለም:: እንዲያውም፥ አባላቱ፥ እራሳቸውን ከናዚና ከፋሽሽቶች ዕልመት ለማዳን ሲሉ፥ ሀገራችንን ለመሥዋዕት ጠቦት አሳልፈው ሰጧት:: ለሙሶሊኒ የመርዝ ጋዝ ዕልቂት የኢትዮጵያን ሕዝብ አጋልጠውት ቀሩ:: ምናልባት ለታሪክ ግንዛቤ ብቻ ሲባል መጥቀስ ካስፈለገ፥ ወረራውን የተቃዎሙ አራት አባል ሀገሮች ቢኖሩ፥ አሜሪካ፥ ሩሲያ ( የቀድሞዋ ሶቭየት ኅብረት) ሜክሲኮና አየርላንድ ብቻ ነበሩ:: ያም ሆኖ፥የኢትዮጵያ የአድኑኝ ተማፅኖና አቤቱታ መና ሆኖ ቀረ:: በወቅቱ ሀገራችን፥ እንደ ደሃ አደግ ሆና ቀረች::

የኢትዮጵያ ድሃ አደግነት እንደገና ከአምሳ ስድስት ዓመታት በኋላ ፥ በአዲስ ሁኔታና የታሪክ አጋጣሚ እንደ ገና ቀጥሏል::

ሀገራችን በዓለም ኅብረተ ሰብ ዘንድ፥ እንደገና ጥቃት የደረሰባትና ህልውና አደጋ ላይ ሲወድቅ እንደ ድሃ አደግ የተቆጠረችበት አጋጣሚ፥ በ1984 ዓ ም ወያኔ ኤርትራን ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል ደብዳቤ ጽፎ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጉባዔ ሲያቀርብ ነበር። ታሪክ በለተለያየ ሁኔታና አጋጣሚ እራሱን ይደግማል እንደሚባለው ሁሉ፥ ይህ ሁኔታ ልክ ከአምሳ ስድስት ዓመታት በኋላ በተመሳሳይ ሂደት፥ ሀገራችን ኢትዮጵያ፥ ተከራካሪና አለሁልሽ የሚላት በመጥፋቱ እንደ ገና የዓለም ፍርደ-ገምድል ብያኔና ግዴለሽነት ሰለባ ሆነች። መልካም አጋጣሚ ሲጠብቁ የነበሩት የኢትዮጵያ የቆዩ ጠላቶችም በወቅቱ የተመድ ዋና ፀሐፊ በነበረው በግብፃዊው ቡጥሮስ-ቡጥሮስ ጋሊ አስተናባሪነት ኤርትራውያን ወገኖቻችን፥ ከወንድም-እህቶቻቸው ኢትዮጵያውያን ጋር እንዲለያዩ ተደረገ። ሀገራችንም በውጭ ኃይል ተፅዕኖ እንደገና እጓለ- ሙታን ሆነች። ዛሬ፥ በድሃ አደግነትም እየተንከላወተች ትገኛለች። ድንበሯን፥ ነፃነቷን፥ ክብሯን፥ ታሪኳንና ሰብዕናዋን ብቻ ሳይሆን፥ ራሷ ጨገሬታዋም እንኳ ሳይቀር እየመነመነ ይገኛል። በድሃ አደግነት የምትጠራሞተው ሀገር፥ ዛሬ ህልውናዋ በሞትና ሽረት መካከል ይገኛል። ብሄራዊ ጥቅሟንም ሆነ ደኅንነቷን የሚጠብቅላት የራሷ የሆነ ብሄራዊ መንግሥት ማጣቷ ብቻ ሳይሆን፥ ከዘረኞች አገዛዝ ነፃ አውጥተን ከጥፋት እናድናታለን የሚሉት የተቃዋሚ ኃይሎችም ቢሆን በራሳቸው ችግር ምክንያት ይህንን ለመፈፀም አለማቻላቸው ነው።

የማነኛውም ሀገር መንግሥት የትኛውንም ባህርይ፥ ቅርፅ፥ ይዘት፥ ድርጊትና ሂደት ሊይዝ ይችል ይሆናል። ሁሉም አንድ የጋራ ማንነት ግን ይኖራቸዋል። ቢያንስ የሀገራቸውን ብሄራዊ ጥቅም ምንም ምን ቢሆን መጠበቅ አለብን የሚል አመለካከት ይኖራቸዋል። አምባገነን ከሆኑም፥ ሕዝቡን ሊፈሩት፥ ሊጠሉት፥ ሊጨቁኑት፥ሀብት ንብረቱን ሊመዘብሩት፥ ልማት ዕድገቱን ሊያጫጩበት፥ ምናልባትም ብሄራዊ ጥቅሙን ለባዕድ አሳልፎ በመስጠት የተኅብዳጅነት ባኅርይና ድርጊት ሊያሳዩ ይችሉ ይሆናል። የሀገራቸውን ሕልውና ሲያጠፉ፥ድንበር ሲያስደፍሩ፥ የግዛት ልዕልናን ሲያዋርዱ፥ ታሪክን ባኅልን፥ ቅርስን ዕምነትን፥ ሲያረክሱ የታዩበት የማስረጃ ሰነድ ግን መኖሩን እንጠራጠራለን። አብሶማ የለየላቸው አምባገነኖች፥ የሀገራቸውን ሕልውና በመጠበቅ በኩል ቀናዒ እንደሆኑ ይነገርላቸዋል። በአረመኔነቱ በታሪክ ተወዳዳሪ የማይገኝለት አዶልፍ ሂትለር እንኳን፥ የሰውን ዘር በማጥፋት ካልሆነ በስተቀር የጀርመንን ብሔራዊ ጥቅም በመሸጥ የሚከሰሰው እስካሁን አልመጣም።

የወያኔ ሥራ ጥንታዊቷን ሀገር አፈራርሶ ወሰኗን እያስደፈረ፥ ኅልውናውን ለማጥፋት ወደ ትንንሽ የጎጥ ክልል መሸንሸን ነው። በዚህም ተባለ በዚያ፥ በምንም መስፈርትና የፖለቲካ ትንታኔ ቢገመገም፥ የዛሪይቱ ኢትዮጵያ ዞሮ ዞሮ እጓለ ሙታን ከመሆን አልዳነችም። እንደ ደሃ አደግ ጥጃ አዛኝና አለሁልሽ ብሎ ሊያድናት የደረሰላት ኃይል አላገኘችም። አርበኞቿ ተበታትነዋል፥ ተከፋፍለዋል። ኅበዛዝቷ፥ ወህኔ ገብተዋል፥ የሃይማኖት ተቋማቷ

ተደይነዋል፥ ገዳማቷ ተዘግተዋል፤ ምዕመኗ ተበታትነዋል፥ ዜጎቿ- ምሁሮቿ ተሰድደዋል፡፡ ደራስያኗ ብዕራቸው ተይዟል፤ የሕዝቧ የአርበኝነት ጎራዴ ወደ ሀፎቱ ከገባ ቆይቷል፥  ዜጎቿ የመሪ ያለህ ፥የነፃ አውጭ ያለህ እያሉ ቢጮሁም ምላሽ አላገኙም፡፡ እስካሁን!

ይህ የኢትዮጵያ ድሃ አደግነትና እጓለ ሙታን መሆን በግድም ሆነ በውድ በአስቸኳይ ሊቆም የገባል፡፡ ሊያቆሙት የሚገባቸውና የሚችሉትም ዜጎቿ ብቻ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ ችግር ባዕዳን ይፈቱታል ብሎ መማሰን ዘበት ነው፡፡ ያማ ቢሆን ኖሮ፥ እስካሁን የተደረገው የቀቢፀ--ተስፋ ድካም ውጤት ባስገኝ ነበር፡፡  ያ አልሆነም፡፡ በውጭ ሀገር ከተሞችና አደባባዮች የተደረጉት ሰላማዊ ሰልፎች፥ የርሃብ አድማዎች፥ የሻማ መብራቶች፥ የተማጽንዖ ደብዳቤዎች፥ የተዘመሩት መፈክሮች፥ የተለቀሱት እንባዎች የታዩት ቁጭቶች-ምሬቶች-ሀዘኖች የተላለፉት ውሳኔዎች፥ ወዘተረፈ እንዲያው በደፈናው፥ ባዶ- ከንቱ ነበሩ ባይባልም፥ ባዕዳን የእኛን ጩኸት ሰምተው ለችግራችን መፍትሄ በመፈለግ የሚጠበቀውን ውጤት ሊያስገኙልን አለቻሉም፡፡  ለምን ይህ አልሆነም? ብሎ መጠየቅና መልስ ማግኘት፤ የእያንዳንዱ ሀገር ወዳድ ዜጋ ኃላፊነትና ግዴታ ነው ብሎ ኢሕአፓ ሊያምን ይፈለጋል፡፡

<u>ኢሕአፓ፥ "ከእኔ በላይ ሀገር ወዳድና አርበኛ ላሳር ነው" የሚል  ከንቱ ትዕቢት ባያስተናግድም፥ የእርሱን ሀገር ወዳድነት በጥያቄ ውስጥ ለማስገባት የሞራል ሥልጣን ያለው የለም  ብሎ ለማለት ግን ትህትና በተላበሰ ሙሉ-ልብነት ለመናገር የሚያስችል ታሪክ አለው፡፡</u>

ይህንን የምንለው፥ የቅድሚያ አጀንዳችን የኢትዮጵያ ሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም ማስከበርና ማስጠብቅ በመሆኑ ብቻ ነው፡፡ ያማ ባይሆን ኖሮ፥ እንደ ወያኔ የሀገራችንን መሬትና ዛፍ ለሱዳን ቸብችበን የሱዳንን ርዳታ  በማግኘት የወያኔን ቁማር መጫዎት ሊያቅተን የሚችል አልነበርም፡፡ የሀገራችንን ጥቅም ለማስከበር ባደረግነው ትግል፥ ከጠባብ ብሄረተኞች በተካሄደው ውጊያ ከባድ መሥዋዕት ከፍለንበታል፡፡ የሀገራችንን ዕውነተኛ ታሪክ በማጣመም  በሀሰት የተሞላ ተረት ለመፃፍ ከሞከሩትም ጋር ተጋፍጠን ዕቅዳቸውን አክሽፈንባቸዋል፡፡  ኢትዮጵያን ዕጓለ ማውታ ሆና እንድትቀር የሚደረገውንም ርብርቦሾ በየቦታው  ዘብ በመቆም ታዳጊነታችንን ከማረጋገጥ ፍንክች የማንል መሆናችንን በነባቢት ሳይሆን በድርጊት አስመስክረናል፡፡

እኛ፥ሀገራችን ኢትዮጵያን እንደ ድሃ አደግ ተምሰሌት  የምንቆጥራትና ሕዝባችንንም ዕጓለ-ሙታን ሆነብን ብለን የምንቆጨው፥ የምናማርረውና የምንተክነው፥ ለአለፉት ሠላሳ አምስት የትግልና የመስዋዕት ዓመታት፥ ከአየነውና ከታዘብነው ተመክሮ በመነሳት ነው፡፡ አንድ በተለይ የምናተኩርበት ሃቅ አለ፡፡ይኸውም ሀገራችንን ከዘረኞች ጥፋት ማዳን የሚችሉት ዜጎቿ ብቻ እንጅ የባዕዳን ጣልቃ ገብነትም ሆነ ተፅዕኖ አለመሆኑን ነው፡፡  ከዚህ ድምዳሜ በመነሳት፥ ኢትዮጵያን ከዕጓለ ሙታንነት ለማውጣት በሚደረገው ሀገራዊ

ትግል፥ ከሕዝቡ ጎን በመሰለፍ የሚጠበቅበትን መስዋዕት ለመክፈል ዛሬም እንደ ትላንቱ ዕምነቱ የፀና መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ይህንንም ቁርጠኝነት፥ እንኳንስ ወገኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ፥ ጠላቶቹ የወያኔ መሪዎችም ሳይቀሩ እያንገፈገፋቸውም ቢሆን የማይክዱት ሀቅ ነው፡፡ በዕርግጥም ኢትዮጵያ ሀገራችን ዕጓለ-ሙታን ሆና አትቀርም፡፡